# ተቆርቋሪ የሌላት ኢትዮጵያ ወደ የት?
# ትብብር ወይንስ ውድድር ?

አክሎግ ቢራራ (ዶር)

የብዙ ሽህዎች አመታት ተከታታይ ታሪክ፤ መንግሥታትና ዝና ያላት ኢትዮጵያ የምትታወቀው ከሁሉም ብሄር፤ ብሄረሰብና ሕዝቦች ተወጣጥተው ግዛታዊ አንድነቷን፤ ነጻነቷን፤ ክብሯን፤ ዘላቂ ጥቅሟንና ሉዐላዊነቷን ባስጠበቁት ጀግኖቿ መስዋእት ነው ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። አፍሪካ፤ የመካከለኛው ምስራቅ፤ የላቲን አሜሪካና ካሪቢያን እና የኤዥያ አገሮች በቅኝ ገዢዎች እጅ ወድቀው ሲማቅቁ፤ ድሃና ኋላቀርም ብትሆን፤ ኢትዮጵያ ነጻነቷንና ሉዐላዊነቷን በራሷ አቅም አስከብራ ለተከታታይ ትውልድ አስተላልፋለች። በጀግኖቿ ትግል ከፋሽስት ወረራ ነጻ ከሆነች በኋላ በዓለም ደረጃ እውቅና ያገኘችው ከሰማይ የወረደ አይደለም።

አገር ወዳድ የሆኑ ልጆቿ ጠንክረውና ተባብረው ስለሰሩ ነው። ለምሳሌ፤ ኢትዮጵያ ሌሎች ታዳጊ አገሮች ገና ከቅኝ ገዢዎች መዳፍ ነጻ ሳይወጡ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ የተባለውን አቅም የሌለው ዓለም አቀፍ ድርጅት ተክቶ በአዲስ መልክ በ 1945 ዓ.ም. የተቋቋመውን የተባበሩት መንግሥታትን ከመሰረቱት አገሮች መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት። ወጣቱ ትውልድ እንዲያስታውሰው የምፈልገው አንድ ነጥብ አፄ ኃይለ ሥላሴ በሊጉ ቀርበው ለአገራቸው ነጻነት ሲሟገቱ ታሪክ የሚያስታውሰውን ንግግራቸውን ከራሳቸው መሰረተ ሃሳብ ጨምቀው ንግግሩን ካዘጋጁት ኢትዮጵያዊያን መካከል ከፍተኛውን ቦታ የያዙት ሟቹ ጠቅላይ ሚንስትር አክሊሉ ኃብተወልድ ናቸው።

የአጼ ኃይለ ሥላሴ አቤቱታ፤ የቀረበው ንግግርና የሰጡት ታሪካዊ ማስጠንቀቂያ ድጋፍ ባያገኝም፤ የተገኘው ትምህርት ከፍተኛ ነበር። ክቡር አቶ አክሊሉ ሊጉ ደካማ ስለሆነ ኢትዮጵያን ለፋሺስቶች ጥቃት እንዳጋለጠ ያውቁ ነበር። የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ከተካሄደ በኋላ፤ የዓለም ጦርነት ተደጋጋሚ እንዳይሆን ከተፈለገ ወደፊት የሚቋቋመው ድርጅት የተለየ መሆን አለበት የሚል እምነት እንደነበራቸው ይጠቀሳል። በአዲስ መልክ የተቋቋመው የተባበሩት መንግሥታት ከሊጉ የተለየና ለጋራ ደህንነት (Collective Security) አስተማማኝ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ካደረጉት መንግሥታት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ነበረች። በተለይ የተባበሩት መንግሥታት አካል የሆነው የደህንነቱ አካልይ (UN Security Council) እንዲመሰረት በተደረገው ጠረት ልይ።

ይኼን ታሪክ የመዘገበውን የኢትዮጵያ አስተዋፆ ስኬታማ ያደረጉት ደርግ በጭካኔ የገደላቸው ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር አክሊሉ ኃብተወልድ እንደነበሩ መረጃዎች ያሳያሉ። እኒህ ከራሳቸው ጥቅምና ዝና ባሻገር ለአገራቸው ነጻነት፤ ክብር፤ ግዛታዊ አንድነት፤ ሉዐላዊነትና ዘመናዊነት ቀን ከሌት ይሰሩ የነበሩ ትሁት፤ ብሩህና አስተዋይ ኢትዮጵያዊ ለአገራቸው ያበረከቱት አስተዋፆ በዚህ የተወሰነ አልነበረም። የአገራቸውን ታሪክ ሂደት መሰረት በማድረግ የወደፊቱ ደህንነቷና ዘመናዊነቷ አስተማማኝ የሚሆነው ጣሊያኖች በመሳሪያ ኃይል ቅኝ ያደረጓት የኢትዮጵያ አካል የነበረችው ኤርትራ ወደ እናት አገሯ ስትቀላቀል ብቻ መሆኑን የተገነዘቡ መሪ ነበሩ።

ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ የዲፕሎማሲ እውቀትና ጥበብ አስፈላጊ መሆኑን የተገነዘቡት እኒህ የታወቀው የፈረንሳይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሶቦርን ምሩቅ፤ ታሪካቸው እና ለአገራቸው ያበረከቱት ግዙፍ አስተዋፆ በሚገባ ያልተመዘገበና እኛ ኢትዮጵያዊያን እንደ ጥሩ ምሳሌ ልንጠቅሳቸው የሚገባ አገር ወዳድ ናቸው። በእኔ ግምት፤ ሌሎች አገሮች እንዳደረጉትና አሁንም እንደሚያደርጉት የኢትዮጵያ ተከታታይ ትውልድ የእኒህን አገር ወዳድ ታሪክና ልዩ አስተዋፆ ለማስታወስ ኃውልት ቢሰራላቸው አግባብ ይኖረዋል። ኢትዮጵያ እንድትጠፋ ሆነ ተብሎ የተደረገው፤ አሁንም የሚደረገው አገር ወዳዶችን በማጥፋት ነው።

ስለሆነም፤ ይህ ወንጀል በተካሄደባት ኢትዮጵያ እንደሳቸው ያሉትን ማስታወስ አግባብ አለው። ከጀርባ ሆነው፤ ሌሎችን፤ በተለይ የታባበሩት መንግሥታት አባላት አገሮችን በማሳመን ያደረጉት የተቀደሰ ተግባር ውጤት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ተመልሳ እንድትቀላቀል ማድረጋቸው ነው። ይኼን ታሪክ የመዘገበው የብዙ መቶ ሺህ ኢትዮጵያዊያን ህይወታና ንብረት የወደመበት የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት እንዲፈርስና ኢትዮጵያ ለጥቃት እንድትጋለጥ ያደረጉት ህወሓትና ሻቢያ ናቸው። ይህ ክህደት አገሪቱን ለጥቃት አጋልጧታል።

የባህር በሯ ከተዘጋ በኋላ የሌሎች ጥገኛ ሆናለች። በተጨማሪ፤ ኢትዮጵያ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ያላት ግንኙነት ጠንካራ እንዲሆን ካደረጉት ኢትዮጵያዊያን መካከል አንዱ ናቸው። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አዲስ አበባ ላይ እንዲቋቋም አገሪቱ ካላት የተወሰነ ኃብት ቀንሳ እንድታበረክት ማድረጓን ታሪክ ያስታውሳል።

ምጣኔ ኃብቷን ተጠቅማ ለአፍሪካዊያን ነጻነት አስተዋፆ አድርጋለች። 2 ጠቅላይ ሚንስትሩ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ነጻነት፤ ግዛታዊ አንድነት፤ ዘላቂ ጥቅምና ሉዐላዊነት አስተማማኝ የሚሆነው ኢትዮጵያ ዘመናዊ ኢኮኖሚ ሲኖራት፤ ሕዝቧ ከድህነት፤ ከረሃብና ከጥገኝነት ራሱን ነጻ ሲያወጣ ብቻ መሆኑን የተገነዘቡ በራሳቸውና በሃገራቸው ሕዝብ እምነት የነበራቸውና የኋላውን ትምህርት አድርገው የወደፊቱን ለመቀየስ ያልተቆጠበ ጥረት ያደረጉ አስተዋይ ግለሰብ ነበሩ።

የተባበሩት መንግሥታትን ለመመስረት ለተደረገው ጥረት ኢትዮጵያዊያን ወደ ውጭ የሚጓጓዙበት የራሳቸው አየር መንገድ የላቸውም ነበር። የሚጓጓዙት በአሜሪካኖች ቾርታና አውሮፕላኖች ነበር። ይኼን ግልጽ የሆነ የእድገት ክፍተትና ተግዳሮት መቋቋም ብሄራዊ ግዴታችን ነው ብለው ያመኑት አክሊሉ የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲቋቋም ከፍተኛ አስተዋፆ ያደረጉበት ምክንያት ይኼው ነው። አየር መንገድ ዘላቂ ብሄራዊ ተቋም ነው፤ እንዲሁ በምኞት አይመሰረትም። የአቅም ግንባታ ያስፈልገዋል። ሜካኒኮች፤ አውሮፕላን አብራሪዎች፤ አስተናጋጆች፤ ጠጋኞች ወዘተ ያስፈልጋሉ።

ለዚህ አመቻች የሆነው ከአሜሪካው ትራንስ ወርልድ አየር መንገድ ጋር የተደረገው ስምምነት ነበር። በተፈጥሯቸው አገር ወዳድና በፍጥነት ለመማር የሚችሉት ኢትዮጵያዊያን በአጭር ጊዜ አየር መንገዱ ራሱን እንዲችል አድርገዋል። ዛሬ ህወሓት በበላይነት የሚቆጣጠረውና የሚነግድበት አየር መንገድ የተቋቋመው የተባበሩት መንግሥታት ሲቋቋም ነው።

ዛሬ ኢትዮጵያዊያንን ከአየር መንገዱ አገልግሎት እንዲባረሩ እያደረገ፤ የውጭ ዜጋዎችን ቀጥሮ ከፍተኛ ደሞዝ የሚከፈልበት አየር መንገድ በሰው ኃይል ራሱን ከመቻል ታግቦ ጥገኛና የፖለቲካ መሳሪያ ሆኗል። አገር ተከል ተቋምና እድገት አስፈላጊ ነው የሚለውን መርህ ካስተማሩን ኢትዮጵያዊያን መካከል አክሊሉ ኃብተወልድ ከፍተኛ ቦታ ቢኖራቸውም ዛሬ የሚካሄደው ጎሳዊ ፖለቲካና የተቋማት መዳከም ጥገኝነትን እያጠናከረ ነው።

## ጥገኝነት ኢትዮጵያዊያን የማይቀበሉት የሉዐላዊነት ጸር ነው።

እኒህን አስተዋይ፤ አገር ወዳድና ለኢትዮጵያ እውቅና ያበረከቱ ኢትዮጵያዊ በክፉ ጊዜ ያፈራቸው ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። የፖለቲካ ፓርቲ ወይንም አንድ ጎሳ አይደለም። አጋጣሚ ሆኖ ለጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆን በ 1972 በአካል አነጋግረውኝ ነበር።

በአጭሩ የተማሪው እንቅስቃሴ በጦፈበት እና ተገንጣይ ኃይሎች ስር ሰደው ኢትዮጵያዊያንን እንዲከፋፈሉ ባደረጉበት ቀውጢ ቀን ከአሜሪካ ተመልሸ አገሬን ለመጎብኘትና ወላጆቸን ለመጠየቅ፤ ትዳር ለመያዝና ለዶክተሬቴ ምርምር ለማድረግ ስሄድ ቦሌ እንደደረስኩ ፖሊስ ወደ እስር ቤት ወሰደኝ። ነገሩ ሲጣራ የታሰርኩበት ምክንያት Challenge በተባለው የተማሪዎች መጽሄት በስሜ፤ ማለትም በውሸት "የኤርትራን መገንጠል" እደግፋለሁ የሚል ግዙፍ ድርሰት በራሴ ስም ተጽፎ ለመረጃ ስለደረሰ ነበር። ይኼን ድርሰት ያዘጋጁት እነማን እንደሆኑ አውቃለሁ። ተጠቃሚዎቹ ሻቢያና ሌሎች ተገንጣይ ኃይሎች ነበሩ።

"የውሸቱ ተግዳሮት (The forged Challenge)" በሚል አርእስት ማስተባበያ ጽፌ፤ ሰነዱን በእጀ ይዠ ነበር። የፖሊስ ጣቢው መሪዎች እኔን ስላላመኑኝ ጉዳዩ ለበላይ ባለሥልጣናት እንዲቀርብ ያደረጉልኝ ምንም የማላውቃቸው፤ አሁን "የነፍስ አባቴ" የሆኑት ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው መንፈሳዊ መሪዎችና አባቶች መካከል ከፍተኛ ቦታ የያዙት "አባታችን" አቡነ መልከፀዲቅ ናቸው።

ጠቅላይ ሚንስትሩና የደህንነት ሃላፊው ኮሎኔል ሶሎሞን ከዲር በየተራ በግል አነጋገሩኝ። ጽሁፉን እኔ እንዳልጻፍኩት፤ እንዲያውም በብሄረሰቦች የመገንጠል ጥያቄ ላይ የማያወላውል አቋም እንዳለኝ፤ ዲሞክራሳዊ ስርዓት እንዲመሰረት እንጅ መገንጠልን እንደማልደግፍ፤ የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ገዢ ጥያቄ ሳይሆን የመደብ፤ የአስተዳደር፤ የሰብአዊ መብቶች አለመከበር፤ የዲሞክራሲ አለመኖር ወዘተ ጥያቄ መሆኑን አስረዳሁ።

"ካሰራችሁኝ የመሳፍንቱን አገዛዝ ተቃውመሃል ብላችሁ እሰሩኝ… በኤርትራ መገንጠል ጥያቄ ግን ልታስሩኝ አትችሉም" ብየ ተከራከርኩ። ይህ ለፖለቲካ ጥቅም የሚደረግ የውሸት ፖለቲካ ባህል አሁንም ቀጥሏል። ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ እውቅና አግኝታ አሁንም ፈውዳል፤ ኋላ ቀርና ከሌሎች ነጻ ከሆኑ የአፍሪካ አገሮች--ጋና፤ ኬንያ፤ ናይጀሪያ ወዘተ ጋር ተመጣጣኝ እድገት የማታሳይ መሆኑን ለማሳየት ሞክሬ ነበር። የንጉሰ ነገሥቱ ስርዓት ዘመናዊ ካልሆነ አደጋው እየተባባሰ እንደሚሄድ ጠቅላይ

ሚንስትሩ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች፤ በተለይ ግብጾች አገሪቱ እንዳትቀጥል ጥረት እንደሚያደርጉ ተናግረዋል። እኔም በበኩሌ የውጭ ጠላቶች የሚገቡባቸው ቀዳዳዎች ኢትዮጵያዊያንን በመለያየትና ረቂቅ በሆነ መንገድ በመጠቀም፤ በማሳደድ ኢንዲገደሉ በማድረግ መሆኑን ተጋርተናል። ከሁሉም በላይ ትዝ የሚለኝ ጠቅላይ ሚንስትሩ የማዳመጥ ችሎታ ያላቸው፤ በፈገግታ፤ በትህትና፤ በአስተዋይነትና የወደፊቱን በማሰብ ምክር የሚሰጡ መሆናቸው ነው።

ስለራሳቸው አንድም ጉዳይ አልነገሩኝም። ጭንቀታቸው ስለወደፊቷ ኢትዮጵያ ሁኔታ ነበር። "አንተና ሌሎቻችሁ፤ እኛ እንዳደረግነው ወደ አገራችሁ ተመልሳችሁ ኢትዮጵያን ማገልገል፤ ዘመናዊ ማድረግ" ወዘተ ግዴታችሁ ነው የሚል ምክር ለግሰውኝ ተሰናበትኩ። ይኼን ምክራቸውን ስራ ላይ አውየዋለሁ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፊት ቀርቤ "ይቅርታ" ጠይቁ እንደምለቀቅ ቃል ገቡልኝ። "ይቅርታ" ለምን እጠይቃለሁ አላልኩም፤ ሌላ መዘዝ ላለማምጣት።

የተባልኩትን አድርጌ ከእስር ቤት ተፈታሁ። ቁም ነገሩ የእኔ መታሰር አይደለም። ስንት ኢትዮጵያዊያን ታስረዋል፤ ተገድለዋል፤ ተሰደዋል። ቁም ነገሩ ስለ እኔ አይደለም፤ እኒህ አስተዋይ መሪ 3 የሚመጣው አደጋ የታያቸው መሆኑን ለማስታወስ ነው።

***See DireTube TV: The Untold Story of Aklilu Habte-Wold - NEW! Documentary. http://www.diretube.com/diretube-tv-the-untold-story-of-akliluhabte-wold-new-documentary_d3714ad21.html***

የዚህ ሃተታ መሰረት እኛ ኢትዮጵያዊያን የምንከተለው ጎሳዊ የሆነ የፖለቲካ ባህል ለኢትዮጵያ አፍራሽ መሆኑን ለማቅረብና አስቸኳይ የሆነ ብሄራዊ ውይይት እንዲካሄድ ደጋግሜ ለማሳሰብ ነው።

ባለፉት አርባ ሁለት ዓመታት ከላይ በአጭሩ ያቀረብኩትን የነጻነትና የሉዐላዊነት ታሪክ እንደ ተራ ነገር እያየን አባክነነዋል። ብንቀበልም ብንክድም የእኛ መነታረክ፤ መጨቃጨቅ፤ መጠላለፍ፤ መናናቅ፤ እርስ በርስ አለመተማመን፤ ልዩነቶችን በጨዋነት ለመፍታት አለመፈለግ፤ ራስንና ቡድንን፤ ራስንና ጎሳን፤ ራስንና ኃይማኖትን፤ ራስንና ንብረትን ወዘተ ከአገር በላይ ማስቀመጥ ወዘተ አገራችን እንድታመልጠን ግብአቶች እያደረጉ ነው። ይህ የፖለቲካ ባህል በፍጥነት ካልተለወጠ አገራችን ለማደን አንችልም።

ደርግና ህወሓት ካደረጓቸው ጥፋቶች መካከል የኢትዮጵያን የሰው ኃይል፤ በተለይ አገር ወዳዱንና ዲሞክራቱን እየገደሉና እያሳደዱ ማባከናቸው ነው። እንዴት? ብለን ብንጠይቅ፤ ለሃገራችን ነጻነት፤ ደህንነት፤ ሉዐላዊነትና ዘላቂነት እና ለመላው ሕዝቧ ህብረት የቆሙትን ኢትዮጵያዊያን ግለሰቦችና ተቋሞች አውድመዋል፤ እንዲከፋፈል አድርገዋል። ለምሳሌ፤ ህወሓትና ሻቢያ የሚያኮራ ታሪክና ከፍተኛ አስተዋፆ ያበረከተውን፤ የኢትዮጵያን ስብጥር ሕዝብ የወከለውን የኢትዮጵያን መከላከያ ኃይል አፍርሰዋል። በምትኩ የህወሓትን መከላከያ እዝ ተቋማዊ አድርገዋል።

ይኼን የምልበት ምክንያት፤ የደርግንና የአሁኑን አገዛዞች የፖለቲካ የበላይነት እና ለይቶ የማጥቃት ታሪክ ሁኔታ ቀረብ ብሎ መመርመር ለውይይቱና ችግሩን እንዳንደግመው ስለሚረዳ ነው። ከዚህ ላይ ለማሳሰብ የምገደደው ማንም መንግሥት ለአገር ተቆርቋሪ የሆነውን ትውልድ አጥፍቶ በጎሰኛ ትውልድ ሲተካው የአገር አስተማማኝነትን ለማጠናከርና ዘላቂነትና ተደጋጋፊነት ያለውን ዘመናዊ ሕብረተሰብ ለመመስረት አይችልም። የኢትዮጵያን የወደፊት እድል የሚወስነው ሕዝብ መሆኑ አያከራክርም።

ሆኖም፤ ሕዝብ በጎሳና በኃይማኖት ከተከፋፈለ አገርን የመደገፍና አምርቶ ራሱን የመቻል አቅሙ ደካማ ይሆናል። ከደርግ አገዛዝና ራሱ ባባባሰው ድክመትና ውድቀት በኋላ እንዳየነው ከሕዝብ ዐመጽ የሚመጣ እድል የፖለቲካ ፓርቲዎችና የስልጣን ፈላጊዎች ውሳኔ ብቻ ሊሆን አይችልም። ጥንካሬና ዘላቂነት የሚኖረው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የዜግነቱን መብት ተጠቅሞ ውሳኔ ለማድረግ ሲችል ነው።

## ካልረባ የስልጣን ውድድር ወደ ብሄራዊ ትብብር መሸጋገር ወሳኝ ነው

ኢትዮጵያ የምትባል አገር "አለች ወይንስ የለችም?" የሚለው ጥያቄ አነጋጋሪ መሆኑ እንዴት የፖለቲካ ልሂቃንና ምሁራን ሕዝቡን በጎሳ አደራጅተው፤ ባያደራጁም የገዢውን ፓርቲ የጎሳ ፖለቲካ አጀንዳ እየተከተሉ ኢትዮጵያን ለአደጋ እንዳጋለጧት ያሳያል።

ከደርግና ከአሁኑ መንግሥታት በፊት በማይታሰብ ደረጃ የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ጥይት ሳይተኩሱ ያገኙት እድልና ድል እንደተከሰተ መጠራጠር አይቻልም። ያለፉትን አገር ወዳዶች ከመቃብራቸው የሚቀሰቅስ ክስተት ነው። ለምን እዚህ ደረጃ ደረስን የሚለውን ጥያቄ ሳንሰላስል ባለፉት 25 ዓመታት በስርዓት ደረጃ የተካሄደውን የፖለቲካ፤ በተለይ የሕገመንግሥቱን ሂደት ማንሳት ተገቢ ሆኖ አገኘዋለሁ።

## ETHIOPIA'S CONSTITUTION: CAN IT STAND THE TEST OF TIME? MARCH 11, 2016 ADDISSTANDARD

በተባለው ጋዜጣ ዶር ነጋሶ ጊዳዳ፤ የመጀመሪያው የኢህአዴግ ፕሬዝደንት አገር ወዳድ የሆኑ ግለሰቦችንና ተቃዋሚ ፓርቲዎችን አግልሎ የተመሰረተውን ሕገመንግሥት እንዲህ ሲሉ አቅርበውታል። "ወደኋላ ዞር ብየ ስመለከተው ከፍተኛ ስህተት ያደረግነው ከዚህ ላይ ነው…ቢያንስ ቢያንስ ረቂቁን መልሰን ለሕዝቡ ማቅረብና ድምፅ እንዲሰጥበት ማድረግ ነበረብን። የሕዝቡን ተስፋና ምኞት የሚያንጸባርቅ ወይንም የማያንጸባርቅ መሆኑን መፈተሽ ነበረብን።

***Looking back at it today, I would say this was where the biggest mistake was committed.... we should have presented it back to the people of Ethiopia in a form of referendum where the people could have had the chance to decide on whether what we formulated was according to their wish or not. That we did not do and I believe it was a mistake."***

አንድ የቀድሞም ሆነ የአሁን የአገር መሪና ታዋቂነት ያለው ግለሰብ እንደዚህ በግልጽና በድፍረት ስህተቱን ሲቀበል ዶር ነጋሶ የመጀመሪያው ሳይሆኑ አይቀሩም። በዚህ አጋጣሚ ለዶር ነጋሶ የግሌን አድናቆትና ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለኝን ተስፋ አስመርበታለሁ።

ከላይ ጠቅላይ ሚንስትር አክሊሉ ኃብተወልድን የጠቀስኩበት ዋና ምክንያት በዘመነ ህወሓት/ኢህአዴግ ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ መሪዎች የሌሉ መሆናቸውን ስላየሁ ነው። ህገመንግሥቱ ጉድለት ያሳየበት ምክንያት ብዙ ቢሆንም ጥቂቶቹን ማቅረብ ተገቢ ነው። አገር ወዳድ ምሁራን፤ አባቶች፤ ባለሞያዎች፤ የቀድሞ ባለሥልጣናት፤ ሕብረ ብሄር ፓርቲዎች እንዳይሳተፉ ተደርጓል። ኢህአፓ፤ መኤሶን፤ ኢዲዩ፤ 4 ኢሰፓ፤ የመምህራን ማህበር፤ የሰራተኞች ድርጅቶች

***...,The All Ethiopian Socialist Movement (AESM), the Ethiopian Workers Party (EWP), and the Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP) should have participated but unfortunately they didn't."***

በወቅቱ ከፕሮፌሰር አስራት የአቤቱታ ድምጽ ውጭ ለኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና ለመላው ሕዝቧ አንድነት የቆመ ኃይል የለም ነበር። የትግል ሜዳው የተሰጠው ለነጻነት ለቆሙት የጎሳ ቡድኖች ብቻ ሆነ። የዚህን አደጋ ቀደም ሲል ለማወቅ ይቻል ነበር። እነዚህና ሌሎች የህብረብሄር ድርጅቶች ቢሳተፉ ኖሮ ህገመንግሥቱ እንደ ጋናና ሌሎች የአፍሪካ አገሮች "የኢትዮጵያ ሕዝብ" የሚል መግቢያ ይኖረው ነበር፤ አንቀጽ 39 አይታሰብም ነበር።

**"የመገንጠል መብትና የመሬት ይዞታ አከራካሪ ነበሩ…**

በእነዚህ አበይት ጉዳዮች ላይ የተደረጉት ውሳኔዎች በሕዝብ ውይይት አይደለም፤ በሽግግሩ መንግሥትና በሚቆጣጠረው ፓርላማ ነው

…***The two questions that I remember vividly: the right to self-determination, which is now Article 39, and the question of land. These were very controversial even for the Commission. So what we did was put two alternative versions for each of these articles and brought the draft constitution to the Transitional Parliament. The Transitional Parliament discussed on that draft and brought it to the Constitutional Assembly for adoption.***"

እነዚህን አዲስ ተቋሞች ማን በጀርባ ሆኖ ይቆጣጠራቸው ነበር? ሻቢያ፤ ህወሓትና ኦነግ ናቸው። አገር ወዳዶች አገርን የሚያፈራርስ አንቀጽ ህጋዊ አድርገው "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፤ ብሄረሰብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ የተጠበቀ ነው" ብለው አገራቸውን ለማፈራረስ ቃል ኪዳን አይገቡም።

ይኼን የሚያደርግ ቡድን ኢትዮጵያን የሚጠላ እንጅ ታሪኩን የሚቀበል አይደለም። አንቀጽ 39 (1). የመጀመሪያው ውጤት ኤርትራ ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል አደረገ፤ እነ መለስ የፈለጉት ሆነ። በዚህ አላቆመም፤ መገንጠል መብት ነው የሚለው ወሳኝ መርህ ህጋዊ ሆነ። ያመቻቸው የኢትዮጵያን ፈራሽነት እንጅ አንድነት እና ሉዐላዊነት አይደለም።

ፈረንጆች እንደሚሉት "You reap what you sow." አንድ ግለሰብ ወይንም ቡድን፤ ወይንም መንግሥት የዘራው ፍሬ ምን ውጤት እንደሚያስከትል አስቀድሞ ማወቅ ግዴታው ነው። የመከፋፈልን ፖለቲካና ባህል የዘራ መከፋፈልን ስኬታማ ያደርጋል። ጥላቻን የዘራ ጥላቻው ወደራሱ እንደሚመጣ አስቀድሞ ማወቅ ግዴታው ነው።

የመገንጠል መብት አለ ከተባለ መገንጠል የሚፈልጉ ኃይሎችን በማባበል ሊገታቸው አይችልም። በተጻራሪው በሕዝብ መካከል የማይታረቅ ልዩነት የለም፤ መደጋገፍ የአንድ ህብረተሰብ ጥንካሬ ምልክት ነው ወዘተ የሚል መልእክትና ትምኅርት ማስተላለፍ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ያጠናክራል። ህወሓት የዘራው ፍሬ ጥላቻን፤ አለመተማመንን፤ መከፋፈልን፤ ስስታምነትን፤ ስግብግብነትን፤ ራስ ወዳድነትን፤ ቂም በቀለኛነትን፤ ዘረኛነትን ወዘተ ነው። የዘራውን ፍሬ እያመረተ ነው። ይኼን ተቋማዊ ያደረገው የአንድን ትውልድ ስነልቦናና አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ በመማረክና በመለወጥ ነው። አማራው ትግራዩን፤ ኦሮሞው አማራውንና ትግራዩን፤ አማርው ኦሮሞውንና ትግራዩን፤ ደቡቡ ኦሮሞውንና አማራውን፤ አፏኩ አማራውንና ትግራዩን ወዘተ ይጠራጠረዋል። በአገር ደረጃ ለመተባበር አስቸጋሪ የሆነው የጎሳው ባህል ጥልቀት ስለያዘ ነው። የኦሮሞው ወጣት በገፍ ሲገደል፤ ሲታሰርና እንዲሰወር ሲደረግ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን ነጻነትና ሰብአዊ መብት እድል ከፍቷል።

ቀደም ሲልና አሁንም፤ አማራው በየቦታው እልቂትና ውርደት ሲካሄድበት ሌላው ዝም ብሎ አይቷል። የአሁኑ መሰረታዊ ጥያቄ አንድ ነው። ይኼን ከሕዝብ እምቢተኛነት እድል ወደ አገር አቀፍ ሕዝባዊ ዐመጽ ለመለወጥ ምን ጎደለን? የሚለው ነው። የሕገመንግሥቱ ችግር የመገንጠሉ መብት አንቀጽ ብቻ አይደለም። በተመሳሳይም ባይሆን በአፍራሽነቱ ማህበራዊ ግንኙነቶችን፤ ተቻችሎ መኖርን፤ ተደጋጋፊነትን፤ ሰጥቶ መቀበልን ወደጎን ትቶ "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፤ ብሄረሰብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው" የሚለው አንቀጽ 39 (3)ን ያጠናከረው የተገንጣይነትንና ያለመቻቻል ፖለቲካን ነው። ራስን በራስ ማስተዳደር ዲሞክራሳዊ መሆኑን እቀበላለሁ። ሆኖም ሚዛናዊ ያልሆነ ራስን በራስ ማስተዳደር ማለት ከመሳፍንት ዘመን በምንም አይለይም። ይህ አንቀጽ በጎሳ መሪዎች ሲተረጎም ማንኛውም የተፈጥሮ ኃብት "የእኛ እንጅ" (ክልል) የሌለው ኢትዮጵያዊ ሊሆን አይችልም የሚል አስጊ የሆነ ውድድርን አስከትሏል።

የብሄረሰብ ማጽዳት ቀላል የሆነበት መሰረት ህገመንግሥቱ ነው። ባይሆን ኖሮ አንቀጽ 32 "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሕጋዊ መንገድ በመረጠው የሃገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቤት የመስራት ነጻነት" አለው የሚለው ሕግ ያለምንም ገደብ ስራ ላይ ይውል ነበር፤ አልዋለም። ከማንነት ጋር እንዲያያዝ የተደረገው የመሬትና ሌላ የተፈጥሮ ኃብት ይገባኛልነት በሕገመንግሥቱም መግቢያ ላይ ተሰምሮበታል።

"እኛ የኢትዮጵያ ብሄሮች፤ ብሄረሰቦች፤ ሕዝቦች" ብሎ ጀምሮ "የራሳችንን እድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፤ በነጻ ፍላጎታችን፤ በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መስርተናል" ይላል። " አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መስርተናል" 5 ሲባል የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ዘጋ፤ በዜግነቱ ብቻ ተቀብለናል ማለት ነው ወይንስ ሌላ? የሕግ የበላይነትን ስራ ላይ የሚውለው ማነውና ለማን? " አንድ ማህበረሰብ" ሲባል ማንን ያካትታል፤ ማንን ለማግለል ያስችላል፤ ይኼንን ማን ይወስናል? ብለን ብንጠይቅ የሚወስኑት ሕገመንግሥቱን የመሰረቱት የጎሳ ልሂቃንና ተተኪዎቻቸው ይሆናሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም። ለምሳሌ፤ አፏክ ያልሆነው ኢትዮጵያዊ በጋምቤላ ለመኖር የሚችለው ህወሓቶችና የህወሓት ደጋፊ የጎሳ ልሂቃን ሲፈቅዱ ብቻ ነው።

ቁጥራቸው በቅጡ ባይታወቅም ብዙ ሚሊየን ኦሮሞ ያልሆኑ ኢትዮጵያዊያን በኦሮምያ ይኖራሉ። እነዚህ ሰብአዊ መብት አላቸው። እንደ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው መብታቸው ምንድን ነው እና ምን ዋስትና አላቸው? በደቡብ ክልሎች የሚኖሩ የትግራይ፤ የጉራጌ የአፋር፤ የኦጋዴን ሶማሌ፤ የአማራ ወዘተ ብሄር አባላት ምን ህገመንግሥታዊ መብት አላቸው? በእነዚህ ክልሎች የሚኖሩ "የውጭ" ተወላጆች (ከጎሳው ውጭ) የመምረጥና የመመረጥ መብት አላቸው ወይንስ የላቸውም? ራስን በራስ ማስተዳደር ማለት ሌላውን ማግለል፤ ሌላውን ከቀዬ ማባረር፤ የሌላውን መብት ማፈን፤ ሌላውን መግደል ሊሆን አይችልም። ይህ ጸረ ሕዝብና ጸረ ዲሞክራሲ ነው። የጎሳ ልሂቃን ይኼን ለመቀበል ችግር ሆኖባቸዋል። "ወደቀድሞው ስርዓት አትውሰዱን" የሚሉም አሉ።

በእኔ ግምት ወደ አፄውም ሆነ ወደ ደርግ ስርዓት እንመለስ የሚል ግለሰብ ወይንም ቡድን የለም። ይኼን በማስረጃ የልተደገፈ የፈጠራ ወሬ ሆነ ብለው የሚያስተጋቡት ህወሓቶችና አጋሮቻቸው ናቸው። ያነጋገርና የአቀራረብ ግድፈት ካልሆነ በስተቀር፤ እኔ እስከማውቀው ድረስ በህበረብሄር ፖለቲካ ውድድር የሚያምኑ ግለሰቦችና ስብስቦች ወደ ኋላዎቹ አገዛዞች እንመለስ

የሚሉ ፈልጌ አላገኘሁ። በአጭሩ ግን "የኢትዮጵያ ብሄሮች፤ ብሄረሰቦች፤ ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ስልጣን (Sovereign Power) ባለቤቶች ናቸው" የሚለው አንቀጽ 8 ያጠናከረው መገንጠልንና በጎሳ መለያየትን ነው።

መገንጠልንም ባይሆን ልክ የደቡብ አፍሪካን የሚመስል አፓርታይድ ወይንም መለያየትን ነው። የጎሳ ክልሎች "የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ስልጣን ባለቤቶች" ስለሆኑ የተለያዩ አገሮች ተፈጥረዋል ወይንም እንዲፈጠሩ ተደርጓል:: ልክ እንደ ደቡብ ሱዳንና ኬንያ ጎረቤት አገሮች እየተመሰረቱ ነው። ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መብቶች መከበር አንጻር ብናየው እነዚህ "ሉዐላዊነታቸው" በህገመንግሥቱ የጸደቀላቸው ክልሎች ሌላውን ለማገልል፤ ለማባረር ቢችሉ አያስገርምም። ራስን በራስ በማስተዳደር ብሂል የሞተው፤ ከኃብቱ የተፈናቀለውና የተሰደደው ሕዝብ ብዛት ግዙፍ ነው።

የመሳሪያ አቅም ያላቸው የሌላውን መሬት ቢነጥቁ አያስደንቅም። ህወሓት የሚከተለው የከፋፍለህ ግዛው፤ በተለይ የማንነት ፖለቲካው ድንበርና ገደብ የሌለው ሆኗል። ሌላው ቀርቶ አማራውን ከአማራው ለመከፋፈልና ለማዳከም ልዩ ዞኖች ተፈጥረዋል። ኦሮሞውን ከኦሮሞው ለመለየት ተመሳሳይ ሁኔታ ቢፈጠር ምን ያስደንቃል።

## የዚህ ውጤት ምን ይሆናል?

ዶር ነጋሶ ያሉት አግባብ አለው። "እኔ የምፈራው ህገመንግሥቱ አሁን ( የእኔ ነጥብ) ካልተሻሻለ አገሪቱን በአንድነት የሚያቆያት ነገር፤ ተቋም ( የእኔ ነጥብ) የለም…ሁኔታዎች ከእጃችን ውጭ ይወጣሉ፤ አገሪቱ ለአደጋ ትጋለጣለች፤ አንድ ነገር መደረግ አለበት…

***I fear if something is not done this constitution will not hold the country together; people will eventually ask why we should have this constitution. If things are not improved, I fear the controversies will get out of hand and eventually put the country's unity in danger. Something has to be done."***

ከላይ እንዳልኩት፤ ከጅምሩ ኢትዮጵያ አስተማማኝ መከላከያ ኃይል እንዳይኖራት ሻቢና ህወሓት በትነውታል። የአንድ አናሳ ብሄር የበላይ እዝ አስተማማኝ የሆነ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም። ማንኛውም አገር ዘላቂነት የሚኖረው ተቆርቋሪ ትውልድ ለማፍራት ሲችል ነው።

በደርግ አገዛዝ የተወለደው፤ ወጣት የነበረውና ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የተወለድውና የተማረው ወጣት ትውልድ ኢትዮጵያን እንዳያውቅ ተደርጓል። የአሁኑ ገዢ ፓርቲ ያስተማረው የአገሪቱን ረጂም ታሪክ፤ የሕዝቧን ተቻችሎ መኖር አይደለም። የጎሳ ፖለቲካን፤ ማንነትንና ክልላዊነትን ነው። ማንነት ብዙ ትርጉም እንዳለው ከዚህ በፊት ባቀርብኳቸው ሃተታዎች አሳይቻለሁ። የአንድን ግለሰብ ወይንም ጎሳ ማንነት መቀበል የሁላችንም ግዴታ ነው። የተለያዩ ዜጎች በሚኖሩበት አገር ማንነት ትርጉምና ዘላቂነት የሚኖረው አንዱ የሌላውን ሰብእነት ሲቀበልና ሲያከብር ነው።

ይኼ ተቀባይነት እንዳይኖረው የምናደርገው ራሳችን ነን። የራሳችን አመለካከት ካልተለወጠ ችግሩ ይባባሳል። የአሁኑን የጎሳ ህገመንግሥት አደጋ ብዙ ምሁራንና ባለሞያዎች ተችተውታል። ከእነዚህ መካከል ጆን አቢንክ ያቀረበውን ጥናት እጋራለሁ። እንዲህ ይላል

***"In contemporary Ethiopia thé discourse of ethnicity has become strongly politicized, more so than ever before, and has created "realities" which did not 6 previously exist. Few of the parties concerned (libération movements which emerged largely in the 1970s and largely "mono-ethnic" political parties dating from the early 1990s) fully realize the artificial aspect of the matter or the implications of their aspirations, especially when they are cast in the inevitable and ubiquitous idiom of "national self-détermination". Neither do they recognize the fact that Ethiopian government discourse on ethnicity, and its political government—be established.***

በአሁኗ ኢትዮጵያ ስለ ብሄረሰብ የሚነገረው ሁሉ ፖለቲካዊ ሆኗል፤ ከመቸውም በበለጠ ደረጃ አዲስ ሃቆችን ፈጥሯል። በ 70 ዎቹ የተመሰረቱት የብሄር ነጻ አውጭ ግንባሮችና በ 1990 ዎቹ የተቋቋሙት የብሄር ፖለቲካ ፓርቲዎች የፈጠሩት ሰው ሰራሽ የፖለቲካ ባህልና የራስን እድል በራስ የመወሰን ሕጋዊ መብት የሚያስከትለውን አደጋ በሚገባ አላወቁትም። የኢትዮጵያ

መንግሥትም የተከተለውና ስራ ላይ ያዋለው መርህና ተቋም የአገሪቱን የወደፊት እድል ወደየት እንደሚያመራ አላጤነውም” ይልና በዚህ ይደመድማል።

***“The issue of recognizing ethnic diversity in a polyethnic polity like Ethiopia deserves much attention. The present government has made a serious effort, although its societal and institutional basis for constitution-making, and for decision-making in general has been slim. There is no going back to a unitary state structure in Ethiopia which denies ethnoregional différences and rights, or which lets one group dominate the state. The formula of ethnicization (although in a different, more effective, fédéral form) should perhaps be encouraged if, first, it is generally interpreted and implemented as libération and democratization; secondly, it is sustained also in the domain of respecting individual human rights within the ethno-regions; thirdly, it works in the economie domain: and finally, it is a tendency and a frame of mind accepted by the "rural masses", the majority. If, however, all this does not happen and if the ethnic emphasis combined with economie problems would instead lead to ethnocentrism, regional economie disparities and a reproduction of inequalities on the intermediate level of the new ethno-regional states, then one wonders what is new, and whether the Ethiopian people have won anything yet by the constitutional récognition of their being ethnically separate.” JON ABBINK, Journal of African Law, 41: 159-174 ETHNICITY AND CONSTITUTIONALISM IN CONTEMPORARY ETHIOPIA.***

በአጭሩ “ኢትዮጵያ ወደኋላ መመለስ አትችልም….የብሄረሰብ ፖለቲካ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ እስከሆነ ድረስ አግባብ አለው። ይኼም መደገፍ ያለበት በሁሉም ክልሎች የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ግለሰቦች ሰብአዊ መብት በሕግ ሲከበር ነው፤ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የኢኮኖሚ መብትና ተሳትፎ ሲከበር ነው፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ተስማምቶ ሲቀበለው ነው… ይኼ ካልሆነና የጎሳ ፖለቲካው ትኩረት ከኢኮኖሚው ችግሮች ጋር (ለምሳሌ ድህነት፤ ረሃብ፤ ስራ አጥነት)፤ በሕዝቦችና በክልሎች መካከል ከሚታየው የተዛባ እድገትና በዜጎች መካከል ከተከሰተው (የሚዘገንን) የገቢና የኑሮ ልዩነት ጋር ተደማምሮ ከቀጠለ እኔ የምደመድመው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ አገዛዝ ያገኘው አዲስ ጥቅም የለም” የሚል ነው። የህገመንግሥቱ ተጠቃሚዎች የህወሓት የበላዮች፤ ቤተሰቦችና አጋሮች መሆናቸው በብዙ ማስረጃ ቀርቧል። ደራሲው እንደሚለው የጎሳው ፖለቲካ ፍትሃዊና ዲሞክራሳዊ አይደለም፤ ለሁሉም ዜጎች፤ ብሄሮች ጥቅም አላገለገለም።

ለማጠቃለል ዛሬ ያለው አደገኛ የፖለቲካ ቀውስ ከልዩ ልዩ አቅጣጫዎች በፉክክርና ውድድር ይንጸባረቃል፤

- የፖለቲካ ስልጣን ሽሚያና ውድድር
- የመገንጠል መብት ውድድር
- የተፈጥሮ ኃብት ባለቤትነትና ማንነት ውድድር
- የውጭ ኃይሎች የበላይነት ውድድር
- የኃይማኖት የበላይነት ውድድር **(**ሳውዲዎች፤ ካታሪዎች፤ ኢራኖች፤ ፓኪስታኖች፤ ግብጾች ወዘተ**)**
- የምሁራንና ልሂቃን ግለሰባዊነትና ቡድናዊነት ውድድር
- የሕብረብሄር ድርጅቶች ድክመት፤ መከፋፈል፤ መጠላለፍና አለመተማመን ወዘተ

ይህ በአገር ብሄራዊ ልእልናና በሕዝብ እኩልነትና የፖለቲካ የበላይነት ላይ ትኩረት ያልሰጠ ውድድር ለገዢው ፓርቲ ድጋፍ እየሰጠ ህልውናውን አራዝሞታል።

ህወሓት፤ ኢህአዴግን ከማውገዝና ከመቃወም ባሻገር ለኢትዮጵያና ለመላው ሕዝቧ አማራጭ አልተፈጠረም። ያም ሆነ ይህ ከፊታችን ላይ የተደቀነው ተግዳሮት አገሪቱን ተባብሮ ከመፈራረስ ማዳንና ሽግግሩን ማመመቻቸት ነው። አገርን ማዳን ስል በኢህአዴግ ውስጥ የተሰበሰቡትንም ኢትዮጵያዊያን ያካትታል። ለማጠቃለል፤ የመንግሥትና ተቃዋሚ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ ስብስቦችና ግለሰቦች በመግባባትና በአንድነት አገሪቱን ከጥፋት ማዳን የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው።

በመግቢያው እንዳሳሰብኩት፤ የጣሊያን ወረራ ሆነ ሌላ ብሄራዊ ተግዳሮት ያስተማረን አገር ከሌለ የእርስ በርስ ግጭት፤ ባርነት፤ ጥገኝነት፤ ኋላ ቀርነት፤ ረሃብና ድህነት የሚቀጥል መሆኑን ነው። ኢትዮጵያ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን የሚሆን መሬት አላት። የጠፋው አብሮና ተከባብሮ የመኖር የፖለቲካ ባህሪና ለአገር ተቆርቋሪ የሆነ ዲሚክራሳዊ መንግሥትና አመራር ነው።

ኢትዮጵያ አለች ወይ? የሚለው ጥያቄ የሚያመራን ተቆርቋሪ መንግሥት፤ መሪዎችና ተቃዋሚ ክፍሎች የሉም ወደሚለው ድምዳሜ ነው። ስለሆነም፤ ለሕዝብ የስልጣን የበላይነት፤ ለፍትህ፤ ለእውነተኛ የሕዝብ እኩልነት፤ ለዲሞክራሲ ምስረታ አብሮና ተባብሮ መቆም ወሳኝ ነው። ዞር ብለን ማየት ያለብን አንድ ክስተት አለ። ይኼውም ሁሉም እንተባበር፤ አብረን እንስራ ወዘተ ሲል አርባ ዓመታት አልፈዋል። ለመተባበር በሚል እምነት ተወያይተን መለያየት የፖለቲካ ልማዳችን ሆኗል።

የጎደለው ክፍተት ዲስኩሩን ተግባራዊ ከማድረጉ ላይ ነው። በመጨረሻ፤ ኢትዮጵያ ከሌሎች የምናወራው ፌዝ ይመስላል። ከማፌዝ በላይ ለመሄድ ከተፈለገ መጀመሪያ አገሪቱን ተባብሮ ከጥፋት አድኖ እነዚህ መርሆዎችና እሴቶች እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆኑ የተለያዩ አመለካከቶችንና አማራጮችን ማስተናገድ ግዴታ ነው። እንደገና ከተለመደው የፍክክር ባህል መጥቀን ወጥተን የጋራ አገራችን ከመፈራረስ አድንነን ወደሚቀጥለው የማይቀርና ወሳኝ ወደሆነው አገር አቀፍና የተቀነባበረ ሕዝባዊ፤ ዲሞክራሳዊ ትግል እንሸጋገር እላለሁ።

***http://www.ethiopanorama.com***